# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org



ድርጅት ኃይል ነው። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በኢትዮጵያችን ውስጥ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ እንዲኖር የሚመኙ ዜጎች ሁሉ የሚሰባሰቡበት፤ ወያኔን አስወግዶ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን ማድረግ የሚችል፤ በዲሞክራሲያዊ እሴቶች ላይ የተመሠረተ፤ ቀልጣፋ፣ ስኬታማና ዘመናዊ አሰራርን ተግባራዊ ያደረገ፤ በየጊዜ እየተሻሻለና እየዘመነ የሚሄድ ድርጅት መሆኑ ይቀጥላል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የብአዴን አመራሮች ከግንቦት7 የኦህዴድ ደግሞ ከኦነግ ጋር እያበሩ ነው ሲል አዲሱ ለገሰ ክስ አቀረበ

የአማራ ህዝብ በወያኔ ዘረኞች ሲናቅ፤ ሲሰደብ፤ ሲገፋና ሲፈናቀል ዝም ብሎ ይመለከት የነበረዉ አዲሱ ለገሰ ከሰሞኑ ጌቶቹን ለማስደሰት ሲል የአማራና የኦሮሞ መሪዎችን መክሰሱ ተሰማ። ይህ ከለየላቸዉ የአማራ ህዝብ ጠላቶች ጋር በመሆን የራሱን ወገኖች ሲያሳድድና ሲያስገድል የከረመዉ ወንጀለኛ ሰዉ እስካሁን የሰራዉ ወንጀል አልበቃ ብሎት ከሰሞኑ የብአዴንንና የኦህዴድን መሪዎች ከፈረደበት የግንቦት 7 ንቅናቄ ጋራ በማያያዝ አገዛዙ እርምጃ እንዲወስድባቸዉ ተማጽኗል። አዲሱ ለገሰ በቅርቡ ለኢህአዴግ ምክር ቤት ባቀረበዉ ሰነድ ላይ ኢህአዴግ የአመራር ችግር እንዳጋጠመው፣ የትራንስፎርሜሽኑ እቅድ አለመሳካቱ እንዲሁም በጋምቤላ ተማኝ መሪ መጥፋቱ ተዝርዝሯል። በሃምሌ ወር መጨረሻ የተዘጋጀው ሰነድ ግልባጭ ለጠ/ሚኒስትሩ አማካሪዎች ለአቶ በረከት ስምኦን፣ ለአቶ ደስታውና ለአቶ ኩማ ደመቅሳ ተደርጓል። የቀድሞው ም/ል ጠቅላይ ሚኒስትርና የኢህአዴግ የፖሊሲ ስልጠና ክፍል ሃላፊ የሆኑት አቶ አዲሱ ለገሰ "የኢህአዴግን ተቃዋሚ ሃይላት ማንኮላሻ አቅም ግንባታ እና የአመራር ግንባታና የትራንስፎርሜሽን ጉዞ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ የፖሊሲ አማካሪዎች የቀረበ የሚለው ባለ 39 ገጽ ጽሁፍ፣ ኢህአዴግ ከላይ እስከታች የአመራር ችግር እንደገጠመው በዝርዝር ያቀርባል። ጽሁፉ በመግቢያው "አገራችንን በፈጣን ቀጣይነት ያለውና ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት የእድገት ጉዞ ከድህነት አላቆ በተራዘመ ሂደት ከበለጸጉት አገሮች ጎራ ለማሰለፍ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል አላማ፣ ስትራቴጂ ስልቶችና ፖሊሲዎችን መቀየስ ይጠይቃል። በሌላ አነጋገር አቅጣጫውን በትክክል የሚያመላክት መስመር መቀየስ የትራንሰፎርሜሽን ስኬት የመጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ ነው። መስመሩን ለመቀየስ ይህንኑ ማድረግ የሚችል ብቃት ያለው አመራር ይጠይቃል። ኢህአዴግ በዚህ ፈተና ውስጥ ነው።" ብሏል።

( ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

## እንግሊዝ የኢትዮጵያን ጉዳይ አስፈጻሚ አስጠርታ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጉዳይ አነጋገረች

የግንቦት7 ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በየመን የጸጥታ ሃይሎች ከተያዙ በሁዋላ ሰቆቃ እየተፈጸመባቸው ያለፉት 44ቀናትን በደብረዘይት አየር ሃይል እስር ቤት ውስጥ ካሳለፉ በሁዋላ የብሪታንያ መንግስት የኢትዮጵያን ጉዳይ አስፈጻሚ አስጠርቶ በጽህፈት ቤቱ አነጋግሯል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማርክ ሲሞንድስ አቶ አንዳርጋቸው የኮንሱላር አገልግሎት በአፋጣኝ እንዳያገኙ መደረጉ እንዳሳሰባቸው ለኢትዮጵያው ዲፕሎማት ተናግረዋል። የኢትዮጵያ መንግስት ከዚህ ቀደም ለአቶ አንዳርጋቸው የኮንሱላር አገልግሎት እንደሚፈቀድ ቃል ገብቶ የነበረ ቢሆንም፣ የገባውን ቃል አለማክበሩን የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ መግለጫ ያመለክታል።

ሚ/ር ሲሞንድስ የኢትዮጵያ መንግስት በአፋጣኝ የኮንሱላር አገልገሎቱን እንደሚፈቅድ እንዲሁም አቶ አንዳርጋቸው በሌለበት የተላለፈው የሞት ፍርድ ተግባራዊ እንደማይሆን ማረጋገጫእንዲሰጥ የኢትዮጵያው ዲፕሎማት መልእከቱን ለመንግስት እንዲያስተላለፍ አሳስበዋል።የብሪታንያ መንግስት ያወጣውን መግለጫ በተመለከተ አስተያየታቸውን የጠየቅናቸው የአቶ አንዳርጋቸው ባለቤት ወ/ሮ የምስራች ሃይለማርያም፣ ለህዝብ ይፋ የሆነው መግለጫ በዲፕሎማሲቋንቋ ጠንካራ የሚባል መሆኑን ገልጸው፣ የብሪታንያ መንግስት ተጨማሪ ግፊቶችን እያደረገ ነው ብለዋል። ከዲፕሎማቶች አካባቢ የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው የእንግሊዝ መንግስት የኢትዮጵያን ዲፕሎማቶች እየጠራ በተደጋጋሚ ያነጋገረ ሲሆን፣ ዲፕሎማቶችም አቶ አንዳርጋቸው የኮንሱላር አገልግሎት በአስቸኳይ እንደሚያገኙ ቃል ገብተው ነበር። ይሁን እንጅ ቃላቸውን ለመጠበቅ ያልቻሉት የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች፣ የብሪታንያ ባለስልጣናት ፊት ሲቀርቡ የሚናገሩት እንደሌላቸውና"መልእክት እናስተላልፋለን" የሚል ቃል ብቻ እንደሚናገሩ ለማወቅ ተችሏል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

## የመለስ ፋውንዴሽን የገንዘብ ስብሰባ ህዝቡ እንዳይቆጣ በሚል ላልተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ተደረገ

በኢትዮጵያ ህዝብና በግዛት አንድነቷ ላይ ሃያ አመት ሙሉ ሲያሾፍና ሲቀልድ የቆየዉን ግለሰብ የኢትዮጵያ ህዝብ ለምን ማስታወስ እንደሚገባዉና ለምንስ ለዚህ የለየለት የህዝብና የአገር ጠላጥ ፋዉንዴሺን እንደሚሰሰራለት ባይታወቅም ህዝብ የሚቅመስዉና የሚልሰዉ ባጣበት በአሁኑ ወቅት ለመለስ ፋዉንዴሺን ገንዝብ አዋጣ መባሉ ግን ህንብን ለአመጽ የሚጋብዝ በደል መሆኑን ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ። የመለስ ዜናዊን ፋውንዴሽን እንሰራለን በሚል ኢትዮጵያውያን ሰራተኞችና አርሶአደሮች በነፍስ ወከፍ ከ50 ጀምሮእንዲያዋጡ መገደዳቸው በቅርቡ ከተደረገው የደሞዝ ጭማሪ ጋር ተያይዞ የህዝቡን ቁጣ ሊያባብሰው ይችላል ተብሎ በመሰጋቱ ፣ የገንዘብ መሰብሰቡ ሂደት ለጊዜው እንዲቋረጥ መደረጉን የኢህአዴግ ምንጮች ገልጸዋል። ፋውንዴሽኑን ለማሰራት ከሚፈለገው ገንዘብ 10 እጥፍ እንደተሰበሰበ የሚነገርለት ፋውንዴሽን በወ/ሮ አዜብ መስፍን የሚመራ ሲሆን እስካሁን ድረስ ወጪና ገቢውን በተመለከተ ለህዝብ ለማሳወቅ ባለመድፈሩ ከድርጅቱ አባሎች ትችቶች እየቀረቡበት ነው።

በአዲስ አበባ ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ምሬት ያስከተለው ይህ የገቢ ማሰባሰቢያ ባለፉት ሁለት ሳምንት በድርጅቱ ደጋፊዎች አማካኝነት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ደረሰኝ መያዝ በከተማው ሁሉም ቀበሌዎችና በአንዳንድ የወረዳ የመንግስት መ/ቤቶች ሲዘዋወሩ የታየ ቢሆንም፣ በዚህ ሰሞን ደግሞ በደመወዝ ጭማሪው ቅር የተሰኘው ህዝብ ብሶት ላለማባባስ በሚል ለጊዜው ዘመቻው እንዲረግብ ተደርጓል። ዘመቻው የህዝቡ ምሬት "ቀንሷል" ተብሎ ሲታመን ሊቀጥል እንደሚችል መንጮች አክለው ገልጸዋል። በቅርቡ የተደረገው የደሞዝ ጭማሪ የኑሮ ውድነቱን እያባባሰው መሆኑን በእየለቱ የሚወጡ መረጃዎች ያሳያሉ።

## የአርባ ምንጭ ከተማ የሰማያዊ ፓርቲ መሪዎች ታሰሩ

ስራዉ ማሰር፤ መግረፍና መግደል ብቻ የሆነዉ ዘረናዉ የወያኔ አገዛዝ የዞኑ ፖሊሶች ትናንት ከሌሊቱ 10 ሰአት ላይ ወደ ሰማያዊ ፓርቲ የአርባ ምንጭ አመራሮች መኖሪያ ቤት በመሄድፍተሻ ካደረጉ በሁዋላ ፣ አመራሮችን ወስደው አስረዋቸዋል። የፍርድ ቤት ማዘዣ ይዘናል በማለት ፍተሻ ያካሄዱት ፖሊሶች በአንደኛው ቤት ውስጥ ሁለት ፍሬ ጥይቶችን ማግኘታቸውን ሲያስታውቁ፣ በሌሎች መኖሪያ ቤቶች ደግሞ ቪዲዮ ካሜራዎችን፣ ፊልሞችንና የተለያዩ ወረቀቶችን ሰብስበው ወስደዋል። የአንደኛው አመራር የቅርብ ሰው የሆነ ለኢሳት ሲናገር፣ ፖሊሶቹ ጠመንጃ በሌለበት ሁለት ጥይቶችን አገኘን ማለታቸው አስቂኝ ነው ካለ በሁዋላ፣ ሁለቱንም ጥይቶች ፖሊሶች ራሳቸው ይዘው መምጣታቸውንና አገኘን ብለው መናገራቸውን ገልጿል።

ሉሉ መሰለ፣ በፈቃዱ አበበ፣ ነጻነት መተኪያና ኢ/ር ጌታሁን በየነ የተባሉት አመራሮች ገሚሶቹ በአርባ ምንጭ ከተማ ቀሪዎቹ ደግሞ ከከተማው ወጣ ብሎ በሚገኝ እስር ቤት መታሰራቸው ታውቋል።ኢህአዴግ መራሹ መንግስት የሰማያዊ ፓርቲ የምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ የሆነውን አቶ የሽዋስ አሰፋን እንዲሁም የፓርቲው አባል የሆነቻውን ወይንሸት ሞላን በቅርቡ ማሰሩ ይታወሳል። መንግስት በሽብር ሰበብ ካለፉት ሁለት ወራት ጀምሮ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ይዞ አስሯል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## አፍሪካ እየተመነደገች ነው ሲሉ ፕ/ት አቦማ ተናገሩ

የዛከ40 በላይ አፍሪካ መሪዎችን በአንድ ጊዜ ጋብዘው በማነጋገር ላይ ያሉት የአሜሪካው መሪ ፕ/ት ባራክ ኦባማ አፍሪካ እያደገችና ጠንካራ አህጉር እየሆነች መሆኑን ተናግረዋል። ከዚህ ቀደም እንደነበረው ሳይሆን አፍሪካ በአለም ላይ ተጽእኖ ፈጣሪ መሆን መጀመሩዋን ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል። የአፍሪካ ስኬት ከወጣት ህዝቦቿ ጋር የተያያዘ መሆኑንም ፕሬዚዳንቱ አክለዋል። አሜሪካ በአፍሪካ የጸጥታ ስራ ለመስራትና ለኢንቨስትመንት 14 ቢሊዮን ዶላር መመደቡዋን አስታውቀዋል። ይህ ገንዘብ ቻይና በአፍሪካ ኢንቨስት ካደረገቻው ጋር ሲተያይ እጅግ አነስተኛ መሆኑን ተንታኞች ይናገራሉ። የአሜሪካ ዋና ፍላጎት ቻይና በአፍሪካ ላይ እየፈጠረችው ያለውን ተጽእኖ መቀነስ መሆኑን የሚገልጹት ተንታኞች፣ አሜሪካ ለረጅም ጊዜ ይዛ የቆየችውን" የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች" መስፈርትን ወደ ጎን በማለት ከአንባገነን የአፍሪካ መሪዎች ጋር ቀረቤታ መፍጠሩዋ፣ በቀሪው አፍሪካ ህዝብ ዘንድ ሊያስጠላት እንደሚችል ያስጠነቅቃሉ።

ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ደጋፊዎችን የማሰባሰብ ጥረት

የንቅናቄዓችን ዋና ፀሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ጨምሮ በህሊናና የፓለቲካ እስረኞች ሁሉ ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ መክበድ፤ በፀረ-ሽብርተኝነት ስም በሕዝብ ላይ የሚነዛው ወያኔያዊ ሽብር መብዛት፤ እስሩ፣ እንግልቱ፣ መሳደዱ፣ የሀብት ዘረፋው በየዕለቱ እየጨመረ መምጣት እና ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ኑሮ እየከበደ መምጣቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ጋር ወሳኝ የሆነ ትግል መግጠሚያ ወቅት ላይ መደረሱ አመላካች ሆኗል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል መንፈስ መነሳሳት በተጨባጭ ከሚያረጋግጡ አመላካቾች አንዱ የግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አባል ለመሆኑ የሚፈልጉ ዜጎች ቁጥር በከፍተኛ መጠን መጨመር ነው። ይህንን ለውጥ ተከትሎም ግንቦት 7 የአባላት ቅበላን ሥራ ለማፋጠን የሚረዱ እርምጃዎች ወስዷል። ሆኖም ግን በአባላት ቅበላ ወቅት ሊታለፉ የማይችሉ ጥንቃቄዎች መኖር እንዳለባቸው ደጋፊዎችም እጩ አባላትም ይረዳሉ ተብሎ ይታመናል።

በዚህም ምክንያት አሁንም እየጨመረ የመጣን ንቅናቄውን የመቀላቀል ፍላጎትን ለማስተናገድ፤ ለተግባራዊ ሥራዎች የተነሳሱ፣ ዓላማችንና ንቅናቄዓችንን የሚደግፉ ሆኖም ግን በተለያዩ ምክንያቶች በድርጅት አባልነት መቀላቀል የማይችሉ ወይም የማይፈልጉ አባላትን ለማሳተፍ የሚረዳ መዋቅር ማዘጋጀት ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል። ስለሆነም እነዚህን ወገኖቻችን የትግላችን አካል ብቻ ሳይሆን የንቅናቄዓችንም አካል ለማድረግ እንዲቻል በአባላት ጉዳይ ሥር የደጋፊዎች ማስተባበሪያ መዋቅር እንዲደራጅ ተደርጓል። ይህ አደራጀት ግንቦት 7ን ለማዘመን እና ለኢትዮጵያዊያን ሁሉ የተመቸ ድርጅት ለማድረግ የሚደረገው ጥረት አካል ነው። ይህ አደረጃጀት በአንድ በኩል የድርጅቱን ምስጢራዊት ለመጠበቅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ ባሉ ፍላጎቶች መካከል ያለውን ቅራኔ ለመቅረፍ የቀረበ መፍትሔ ነው።

በዚህም መሠረት በአባልነት ለመመዝገብ ስለእናንተ ምስክርነት መስጠት የሚችል የግንቦት 7 አባል ማቅረብ ለጊዜው ያልቻላችሁ፤ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የግንቦት 7 ደጋፊ እንጂ አባል መሆን የማትፈልጉ ወገኖቻችን ግንቦት 7 ፍላጎታችሁን የሚያሟላ መዋቅር ማዘጋጀቱን በይፋ ያበስራል።

የግንቦት 7 ደጋፊ በግንቦት 7 የውስጥ ጉዳዮች የመወሰን፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት አይኑረው እንጂ የንቅናቄው ሙሉ ተሳታፊና ባለቤት በመሆኑ በልበ ሙሉነት "እኔም ግንቦት 7 ነኝ" ማለት ይችላል። የግንቦት 7 ደጋፊ እንደማንኛውም አባል ድርጅታዊ ሥራዎች ሊሰጡት ይችላል።

በደጋፊነት ለመመዝገብ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ኢሜል፣ እድሜ፣ ጾታ፣ ከተማና የሚኖርበት ሀገር ብቻ የሚጠይቅ የድህረ ገጽ ቅጽ መሙላት ያስፈልጋል። ይህ ቅጽ በንቅናቄው ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል። ደጋፊዎች እውነተኛ ስማቸውን የመስጠት ግዴታ የለባቸውም። አንድ ደጋፊ በየወሩ የሚፈቅደውንና የሚችለውን ያህል ገንዘብ እንደሚያዋጣ ይጠበቅበታል፤ ይህ የደጋፊነቱ አንዱ መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል። ደጋፊ በሚኖርበት ከተማ በሚደረጉ የትግል እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ይጠበቅበታል፤ ይህም ሌላው የደጋፊነት መገለጫ ነው። ደጋፊዎች የንቅናቄው ሳምንታዊ ጋዜጣና ወርሃዊ ልዩ መልዕክት በግል ኢሜላቸው እንዲደርሳቸው ይደረጋል። ደጋፊዎች በተግባር በሚያሳዩት ተሳትፎ ከአባላት ጋር ቅርርብ በመፍጠር ወደ ከደጋፊነት ወደ አባልነት የሚሸጋገሩትን መንገድ ያመቻችላቸዋል።

በተለያዩ ምክንያቶች ራሳችሁን በህወሓትና ጀሌዎቹ መዋቅር ውስጥ ያገኛችሁና በወያኔ እኩይ ተግባራት የህሊና እረፍት ያጣችሁ የሕዝብ ወገኖች ይህንን መዋቅር ከግንቦት 7 ጋር በምስጢር ለመገናኛነት ተጠቀሙበት። በመከላከያና በፓሊስ እንዲሁም በራሱ በኢሕአዴግ ውስጥ ያላችሁ ወገኖቻችን ይህንን መስመር በግኑኝነት መመስረቻነት ተጠቀሙበት። በወያኔ የስለላ ወዋቅር ውስጥ ያላችሁም እድሉን ተጠቀሙበት።

በድህረ ገጻችን ላይ http://www.ginbot7.org/supporter-form/ በቀጥታ በመመዝገብ የግንቦት 7 ደጋፊ መሆን ይቻላል። ድረገጹ በማይከፈትባቸው ቦታዎች በ supporter@ginbot7.org ይፃፉ።

ድርጅት ኃይል ነው። ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በኢትዮጵያችን ውስጥ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ እንዲኖር የሚመኙ ዜጎች ሁሉ የሚሰባሰቡበት፤ ወያኔን አስወግዶ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን ማድረግ የሚችል፤ በዲሞክራሲያዊ እሴቶች ላይ የተመሠረተ፤ ቀልጣፋ፣ ስኬታማና ዘመናዊ አሰራርን ተግባራዊ ያደረገ፤ በየጊዜ እየተሻሻለና እየዘመነ የሚሄድ ድርጅት መሆኑ ይቀጥላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!**

---

## የብአዴን አመራሮች ከግንቦት7 የኦህዴድ ደግሞ ከኦነግ ጋር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሰነዱ ለአብነትም እነ አቶ መላኩ ፈንታን ማንሳት ይበቃል" ይልና " ይህን ተከትሎ በአገሪቱ ያሉ አመራሮች ለመቀበል አለመቻላቸው እና የኡመድ ኡቦንግ ሃገር መክዳት፣ በጋምቤላ ክልል ያለው አመራር ታማኝና አስተማማኝ አለመሆኑ፣ የአማራ ክልል አመራሮች ከግንቦት ሰባት ጋር የተያያዘ አመራር መገኘት፣ የኦህዴድ አመራር ከኦነግ ጋር በማበር እና በአማራ ላይ የደረሰውን በደል በቸልታ መመልከት" በማለት ይጠቅስና "በአሁኑ ሰአት በትግራይ ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ (የአመራሩ ቸልተኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ)፣ በአፋር፣ በሶማሌ እና በሃረሬ ምርጫውን ማሸነፍ የሚችል አመራር ድምጽ የማግኘት እድል አለው" ብአሎል። ሰነዱ "የትራንስፎርሜሽን ትግል በውል ይጀመራል እንጅ አይጠናቀቅም ቢባልም በስጋት በተቀመጡት ክልሎች አሁንም አፋጣኝ ስራ ካልተሰራ ኪሳራ ሊያመጡ ይችላሉ" ብሎአል። የአመራሩ ደካማነት የትራንስፎርሜሽን ጉዞ ሳይሳካ እንዲቀር አድርጎታል የሚለው ሰነዱ፣ ድርጅቱ ሰዎችን የሚመለምልበትና የሚያሰለጥንበት መንገድም ብዙ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ፣ የምልመላ ዘዴውንና የስልጠና መንገዱን እንዲቀይር ይመክራል። ኢህአዴግን በመሰረቱ አራቱ ድርጅቶች መካከል ያለው ትውውቅ ደካማ በመሆኑ ከከፍተኛ እስከ መካከለኛ አመራር ያሉት በአንድ ማእከል ስልጠና እንዲሰጣቸው እየተደረገ መሆኑንም ተጠቅሷል። ኢህአዴግ እጅግ በጣም የሚበዛው አባሉ አርሶ አደር በመሆኑ፣ የፖለቲካ መሪዎችን በብዛት ለመፍጠር አለመቻሉን የሚጠቅሰው ሰነዱ፣ ከእንግዲህ በዩኒቨርስቲዎችና በከተሞች ላይ ትኩረት ተደርጎ ሰዎችን የመፈለጉ ስራ እንዲጀመር ያሳስባል።

## እንግሊዝ የኢትዮጵያን ጉዳይ አስፈጻሚ አስጠርታ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በሌላ በኩል ግን አቶ አንድርጋቸው የመጎብኘት ፈቃድ እንዲያገኙ ፈቃድ የሚሰጠው አካል ማን እንደሆነ አለመታወቁ ለዲፕሎማቶች ራስ ምታት መሆኑ ታውቋል። አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ ቀደምብለው ኢትዮጵያን ለጎበኙነት የእንግሊዝ ዲፕሎማቶች የገቡትን ቃል ማክበር የተሳናቸው ሲሆን፣ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ዋናው ፈቃጆች ምናልባትም ከጀርባ ያሉ ሌሎች ስውር ባለስልጣናት ሳይሆኑ አይቀሩም። በኢትዮጵያ ውስጥ ስላጣን ላይ ያለውና ውሳኔ የሚሰጠውን ሰው በትክክል ለማወቅ ባለመቻሉ በርካታ ዲፕሎማቶች ግራ እየተጋቡ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

## አፍሪካ እየተመነደገች ነው ሲሉ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ፕሬዚዳንት ኦባማ እሳቸዉ እራሳቸዉ ወያኔን የመሰለ ነብሰ ገዳይና ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ በእቅፋቸዉ ዉስጥ ታዝለዉ ይዘዉ ቻይና በአፍሪካ ከፍተኛ ኢነቨስትመንት አላት ሆኖም የህዝብ ተቀባይነት የላትም ምክንያቱም በሙስና ከተዘፈቁትና ከአንባገነን መሪዎች ጋር የፈጠረችው ግንኙነት ነው ማለታቸዉ ብዙዎችን አስገርሟል።ፐ/ት ኦባማ በመጨረሻው ጉባኤ በመልካም አስተዳደር እና በጸጥታ ዙሪያ ከአፍሪካ መሪዎች ጋር እንደሚመክሩ ተነግሯል።

# የአንዳርጋቸዉ ትዉስታዎች

“በእኛ እምነት ታሪክ ከነባራዊ ሁኔታ ዉጭ በምኞትና በዘፈቀደ አይሰራም። የሚሰራ ቢሆን ኖሮ ነገስታቱና አምባገነኖቹ ዘሬም በዙፋናቸዉ ላይ በተገኙ ነበር። ባለንበት ወቅት የኢትዮጵያ ህዝቦች መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆመዉ ከዚህ ወዴት እንደሚሄዱ ግልጽ ኢየባልሆነበት ሰዐት ሥልጣን ላይ ያለዉም ሆነ የሌለዉም የግሉን የተስፋ ጎዳናን እዉነተኛዉ የወደፊት ጎዳና አድርጎ የሚያይ ከሆነ ዛሬም እንደ ትናንቱ ከታሪክ መማር አልቻልንም ማለት ነዉ”።

“ከዲሞክራሲ ጋር ሲወዳደር ፍትህ ለሚለዉ ጽንሰ ሀሳብ “ኢትዮጵያዊኛ” ቃላቶች ያሉን መሆኑ የሚያስረግጠዉ ነገር ቢኖር ፍትህ ከማንነታችን ጋር የተቆራኘ መሆኑን ነዉ። ኢትዮጵያዉያን ፍትህ ሲጓደል “በህግ አምላክ” ብለዉ በዳያቸዉን ለማስቆም የሚያሰሙት ጩኸት ፍትህ ከፈጣሪያቸዉ የተሰጠ ከሰብዓዊነታቸዉ ተነጥሎ የማይታይ እሴት አድርገዉ እንደሚመለከቱት የሚያመለክት ነዉ። በምድር ላይም ፍትህ የሚሰጥ ዳኛ ጠፍቷል ብለዉ ሲያስቡ እጃቸዉን ወደ ፈጣሪያቸዉ ዘርግተዉ አንተዉ ፍርዱን ስጠና የሚሉት ከፈጣሪያቸዉ ፍጹምነት የሚመነጭ እዉነተኛ ዳኝነት አለ ብለዉ ስለሚያምኑ ነዉ። ከዚህ በላይ ባጭሩ የተባለዉ የሚጠቁመዉ በኢትዮጵያዉያን ባህልና ስነ ልቦና ዉስጥ የፍትህ ጽንሰ ሀሳብ ያለዉን ትልቅ ትርጉምና ቦታ ነዉ”።

የታሪክን ነባራዊነት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ለፍትህ የሚሰጠዉን ከፍተኛ ቦታና ለነጻነት ያለዉን አመለካከት በተመለከተ ከዚህ በላይ ያሰማናችሁን ሁለት አዉዶች በሁለት የተለያዩ መጽሐፎቹ ዉስጥ የጻፈዉ ዛሬ ፍትህ አልባ በሆነዉ የወያኔ ስርዐት ዉስጥ ለፍትህ፤ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ሲል ለፍተኛ ዋጋ እየከፈለ ያለዉ አንዳርጋቸዉ ጽጌ ነዉ። አዎ የፍትህና የነጻነት አርበኛዉ አንዳርጋቸዉ በግልጽ አንዳስቀመጠዉ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ፍትህ እስከነ ስሙ ሙልጭ ብሎ በመጥፋቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ሁለት እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ እባክህ አምላኬ “ወይ ዉረድ ወይ ፍረድ” እያለ ፈጠሪዉን እየተማጸነ ነዉ። በእርግጥም ፍትህ ፈጣሪያችን ያደለን ትልቅ ማህበራዊ እሴት ነዉ፤ ሆኖም ይህንን የፈጣሪ ስጦታ እኛን የመሰሉ ሌሎች ሰዎች መጥዉ ሲቀሙንና እንዳሰኛቸዉ ሰረግጡን አንረገጥም ብለን እራሳችንን ነጻ ማዉጣትና የተቀማነዉን ፍትህ ከወያኔ ዘረኞች ቀምተን መልሰን ማህበራዊ እሴት የማድረጉ ኃላፊነት የእኛ የራሳችን ነዉ እንጂ የፈጣሪ አይደለም። ፈጣሪያችን ፍትህና ነጻነትን አንዴ ሰጥቶናል እነዚህን የፈጣሪ ስጦታዎች እንዳንቀማ መጠበቅና ከተቀማን ደግሞ ታግለን ማስመለስ ያለብን እኛ ብቻ ነን።

አንዳርጋቸዉ ጽጌ <u>የአማራዉ ህዝብ ከየት ወዴት</u> በሚለዉ መጽሐፉ ታሪክ ከነባራዊ ሁኔታ ዉጭ በምኞት ወይም በዘፈቀደ እንደማይመራና ከትናንት ታሪካችን ካልተማርን የምንደግመዉ ትናንትናና ከትናንት ወዲያ የሰራናቸዉን ስህተቶቻችንን አንደሆነ በግልጽ አስገንዝቦናል። ይህ የአንዳርጋቸዉ ማስገንዘቢያ ያነጣጠረዉ ለመብቱና ለነጻነቱ መከበር ለሚታገለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ረግጠዉ እየገዙ ዝንተ አለም መኖር ለሚፈልጉ የወያኔ ዘረኞችም ጭምር ነዉ። ለመሆኑ አንዳርጋቸዉ ከታሪክ አልተማርንም ማለት ነዉ ሲል ምን ማለቱ ነዉ? . . . “አልተማርንም” የሚለዉ ቃል ለአንድ ሰዉ የሚነገር ቃል ሳይሆን ለብዙኋን የሚነገር ቃል ነዉ። በዚህ ብዙኋን ዉስጥ በአንድ በኩል በየዘመኑ እየረገጡ ከሚገዙት የገዢ መደቦች ጋር የሚታገለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝብን ረግጠዉ እየገዙ መኖር የሚፈልጉ የገዢ መደቦች አሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ በ1966 ዓም የፊዉዳል ገዢ መደቦችን አንኮታኩቶ ከጣለ በኋላ ለሚቀጥሉት 17 አመታት ሰዉ በላዉን የደርግ ስርዐት ተሸክሞ ኖሯል። በ1983 ዓም የኢትዮጵያ ህዝብ አሁንም ወታደራዊዉን የደርግ ሰርዐት በህዝባዊ አመጽ ማስወገድ ችሎ ነበር፤ ሆኖም አሁንም ይህ ህዝብ የታገለለት ድል ባለቤት መሆን ባለመቻሉ ዘረኛ አምባገነኖች መዳፍ ዉስጥ ገብቶ ቁም ስቅሉን እያየ ነዉ። አንዳርጋቸዉ ጽጌ ይህንን የጥፋት ዑደት በሚገባ ተገንዝቦ ነዉ ከታሪክ አልተማርንም ብሎ የነገረን።

በ1966 ዓም ጩኸታችን በሙሉ የፊዉዳሉ ስርዐት እንዲፈርስ ነበር እንጂ የምናፈርሰዉ ስርዐት በምን ይተካል ለሚለዉ ጥያቄ መልስ ስላልነበረን በወቅቱ በስራዉ ጠባይ የተነሳ ተደራጅቶ የነበረዉ የወታደሩ ክፍል ስልጣን ተረክቦ አገራችን 17 አመት ሙሉ የደም ባህር ዉስጥ እንድትዋኝ አድርጓታል። የደርግን ስርዐት ለማፍረስ በተደረገዉ ትግል ዉስጥም ከ1966ቱ ስህተታችን ምንም ባለመማራችን መሳሪያ ከታጠቀ ኃይል ሁሉ ጋር ጉሮ ወሸባዬ መዝፈን ጀመርን። ደርግን የሚዋጉ ኃይሎች ሁሉ የህዝብና የአገር ወዳጆች እየመሰሉን በየጫካዉ እየሄድን ተቀላቅለናቸዉና ዛሬ ይሄዉና እኛዉ እራሳችን ያጠናከርናቸዉ ኃይሎች ስልጣን ይዘዉ ካፈረሱት ስርዐት በከፋ መልኩ አገርንም ህዝብንም እያፈረሱ ነዉ። ደርግ ከፊዳሉ ስርዐት ዉድቀት ምንም ባለመማሩ ሃያ አመት ሳይሞላዉ እሱም እንደ ፊዉዳሉ ስርዐት የታሪክ ቆሻሻ ዉስጥ ተጥሏል። ከፊዉዳሉም ከደርግም ስርዐት ዉድቀት መማር ያልፈለጉት የዛሬዎቹ ዘረኞች ደግሞ የማይቀረዉን ዉድቀታቸዉን እየጠበቁ ነዉ። የወያኔ ዘረኞች ከታሪክ አለመማር ካሁን በኋላ ሊገርመን ወይም ሊያጠያይቀን አይገባም፤ እነሱ ወደዱም ጠሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ያስተምራቸዋል። ዛሬ ዋናዉ ቁም ነገር ወይም ትልቁ ጥያቄ እኛ ካለፉት ሁለት ግዙፍ ስህተቶቻችን ተምረናል ወይ የሚለዉ ጥያቄ ነዉ፡፡ ስራችን የወያኔን ስርዐት ማፍረስ ብቻ ነዉ ወይስ ከወያኔ መፍረስ በኋላስ ለሚለዉ ጥያቄ መልስ አለን። ወያኔን እያፈረስን ስንሄድ ከማፍረስ ጎን ለጎን ወያኔን የሚተካ ስርዐት እየገነባን ነዉ ወይስ ሩጫችን ሁሉ ማፍረሱ ላይ ብቻ ነዉ ያተኮረዉ።

የወያኔን ስርዐት ለማፍረስ በሚደረገዉ ትግል ዉስጥ የተቃዋሚ ኃይሎች መሰባሰብና በአንድነት መቆም ቁልፍ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፤ ሆኖም በእኛ እምነት እጅግ በጣም ከባዱና ዉስብስቡ ስራ ወያኔ የፈጠረዉን ዘረኛ ስርዐትና ቆሻሻ ባህል ማፈራረስና በምትኩ ሌላ መገንባት ነዉ እንጂ ወያኔን ማስወገዱ አይደለም። ወያኔ በህዝብ የተጠላና የተተፋ ስርዐት ስለሆነ በራሱ ዉስጥ በሚፈጠር ቀዉስ ወይም በአንድ እራሱን ለህዝባዊ አመጽ ባዘጋጀ ጠንካራ ድርጅት ተጠራርጎ ሊጠፋ የሚችል ድርጅት ነዉ። ለአገራችን ለኢትዮጵያ በጎ የምንመኝና ዛሬ ወያኔን በተለያየ መልኩ የምንፋለም የነጻነት ኃይሎች እጅግ በጣም ሊያሳስበን የሚገባና አገራችን ኢትዮጵያም በቀላሉ የማትወጣዉ ማጥ ዉስጥ የምትገባዉ ወያኔ ከእነዚህ ሁለት መንገዶች በአንዱ ከወደቀ ነዉ። ይህንን ታሪካዊ ጥፋት እዉን ከመሆኑ በፊት መቀየር የምንችለዉ ደግሞ ወያኔ ከወደቀ በኋላ ሳይሆን ዛሬ ለመዉደቅ ሲንገዳገድ ነዉ።

አንዳርጋቸዉ አገራችን ብዙ አደጋዎች ፊቷ ላይ አንደተደቀኑባት በትክክል ካሳየን በኋላ አደጋዎቹን አንዴት መከላከል አንዳለብንም በቃላትና በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በተግባርም በረሃ ዉስጥ ገብቶ መሬት ላይ እየተኛ ያሳየን የተግባር ሰዉ ነዉ። ዛሬ የወያኔ ዘረኞች አንዳርጋቸዉን አስረዉ የሚያሰቃዩት የአንዳርጋቸዉ ዕቅድና የጀመራቸዉ ስራዎች የእነሱን ቆሻሻ ስርዐት ጠራርጎ ኢትዮጵያን እንደሚያጸዳ ከወዲሁ ስለተረዱ ብቻ ነዉ። በእርግጥም አንዳርጋቸዉ የሽብርተኞች ድርጅት መሪ ቢሆን ኖሮ ጨዋዉና አርቆ አስተዋዩ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያሸብረዉ ሰዉ ሲታሰር ደስታዉን ነዉ እንጂ ቁጣዉንና ሀዘኑን አይገልጽም ነበር። የአንዳርጋቸዉ መታሰርና አንደ ማዕበል ገንፍሎ የወጣዉ ህዝባዊ ቁጣ ወለል አድርጎ ያሳየን ነገር ቢኖር አትዮጵያ ዉስጥ አሸባሪዉ ማን እንደሆነ ነዉ።

ወያኔን የሚተካ ጤነኛ አካል ሳናዘጋጅ በጅምላ ወያኔ ይወገድ አንጂ ከዚያ በኋላ ያለዉ አይቸግርም የሚለዉ አባባል አደገኛ አባባል ነዉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ መስማማት አቅቶን ለእነዚህ የቀን ጅቦች የምንሰጣቸዉ ግዜና በየግላችን በተናጠል የምናደርገዉ ጉዞ አገራችን ኢትዮጵያን ከድጡ ወደ ማጡ ይዟት የሚሄድ አጅግ በጣም አደገኛ ጉዞ ነዉ። “እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ” ስንል እናት አገራችን ኢትዮጵያን ከእንደነዚህ አይነት አደጋዎች ለማዳን ምንም አይነት መስዋዕትነት ለመክፈል ተዘጋጅተናል ማለት ነዉ።

የለበስነዉ ልብስ ከመጠን በላይ ሲቆሽሽ ያለን ምርጫ የተዘጋጀ ቅያሪ ካለን እሱን ቀይረን የቆሸሸዉን ማጠብ ነዉ፤ ቅያሪ ካሌለን ግን አዲስ ልብስ መግዛት ነዉ ያለብን እንጂ መቼም ካላበድን በቀር በቆሻሻ የጀቦደ ልብስ ለብሰን አደባባይ አንወጣም። ከ1966ቱና ከ1983ቱ ታሪካዊ ስህተቶች የተማርን ኢትዮጵያዉያንም ማሰብና ማድረግ ያለብን እንደዚሁ ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ ስርዐት ከመጠን በላይ ቆሽሿልና በበረኪና ታጥቦ የሚጸዳ ከሆነ በፍጥነት መታጠብ አለበት፤ አለዚያም ወያኔን ከማስወገዱ ሂደት ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ አዲስ ስርዐት በጋራ መገንባት እንዳለብን ለአፍታም ቢሆን ልንዘነጋዉ የማይገባን ኢትዮጵያዊ አደራ ነዉ።

ዛሬ እጁ በዘረኞች ተይዞ የሚሰቃየዉ አንዳርጋቸዉ ጽጌ የኑሮ ጓደኛዉን፤ አንድ ፍሬ ልጆቹንና ወንድሞቹን ትቶ ከሞቀዉ የአዉሮፓ ኑሮ በረሃ ወርዶ የማደራጀትና የማስተባበር ስራ መስራት የጀመረዉ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸዉን የአገራቸን ዉስብስብ ችግሮች በሚገባ ስለተገነዘበና ያለፉት ስህተቶቻቸን ላለመድገም የቆረጠ ሰዉ ስለሆነ ነዉ። አንዳርጋቸዉ ከታሪክ እንማር ሲል የፍትህና የዲሞክራሲ ትግላችን አላማና ግብ ወያኔን መጣል ብቻ ሳይሆን ካሁን በኋላ በሰላምና በእኩልነት ሊያኖረን የሚችል ስርዐትም መገንባት አለብን ማለቱ ነዉ። አንዳርጋቸዉ ፍትህ የምንለዉ ጽንሰ ሃሳብ ከኢትዮጵያዊ ማንነታችን ጋር የተቆራኘ ነዉ ሲል ይህንን ከማንነታችን ጋር የተቆራኘ ትልቅና እጅግ በጣም አስፈላጊ ማህበራዊ እሴት በዘረኞች ተቀምተን እንኳን ሃያ ሦስት አመት አንድ ምሽትስ ቢሆን እንዴት ተኝተን እናድራለን ማለቱ ነዉ። አንዳርጋቸዉ ለአገራችን አንድነትና ለዲሞክራሲ መብታችን መከበር እስከ ሞት ድረስ መሄድ አለብን ሲል ዲሞክራሲ ያልሞረደዉ አንድነት ወይም አንድነት ያልሞረደዉ ዲሞክራሲ እስካልገነባን ድረስ ትግላችን አያቆምም ማለቱ ነዉ።

ዛሬ በአለም ዙሪያ በአራቱም ማዕዘን ኢትዮጵያዉያን “እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ” በሚለዉ መፈክር ዙሪያ የተሰባሰቡት የአንዳርጋችዉ አላማና የአርባ አመት ጉዞ የእነሱም አላማና የወደፊት ጉዞ ነዉ ብለዉ ስለሚያምኑ ነዉ። “እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ” ማለት እኔም ልክ እንደ አንዳርጋቸዉ ጽጌ፤ እንደ እስክንድር ነጋ፤ ሡላማዊት ሞላ፤ በቀለ ገርባ፤ አንዱአለም አራጌና ዞን ናይን ብሎገርስ የመብት፤ የነጻነት፤ እኩልነትና የአገር አንድነት ጉዳይ ያንገበግበኛልና ለእነዚህ እሴቶች መከበር እኔም አንደነዚህ ጀግኖች ኢትዮጳያዉያን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነኝ ማለት ነዉ።በአለማዉ የሚጸና፤ ለአላማዉ ግብ መምታት የተዘጋጀና በህይወቱ የቆረጠን ሰዉ ደግሞ ከድል ወዲህ ማዶ የሚያቆመዉ ምንም ምድራዊ ኃይል የለም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ከአንዋር መስጊድ ዉስጥ የታሰሩት ሙስሊም ፖሊሶች ከወንጀል ንጹህ ነን አሉ

የታሰርነው ከመስጊድ ውስጥ ስንወጣ የአድማ በታኝ ፖሊስ አባል መሆናችን የሚገልጽ መታወቂያ በማሳየታችንና ፖሊሶች በመሆናችን ብቻ ነው፤» ነዉ እንጂ እንኳን ሊያሳስር ለጥርጥር የሚያበቃም ወንጀል አልፈጸምንም በማለት የተጠረጠሩበትን የወንጀል ተሳትፎ ድርጊት ተቃወሙ። የፖሊስ አባላቱ ተቃውሞአቸውን የገለጹት ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፖሊስ ኮሚሽን ጉዳዮች ጊዜ ቀጠሮ ማስቻያ ችሎት ለአራተኛ ጊዜ ሲቀርቡ ነው።

ኮንስታብል አብዱራህማን የተባለው ተጠርጣሪ ፖሊስ ወንድሙን ለመጠየቅ ሲሄድ የፀሎት ሰዓት ስለደረሰበት አንዋር መስጊድ ሰግዶ ሲመለስ መያዙን ለፍርድ ቤት ተናግሯል። ኢንስፔክተር መሐመድ የሱፍ ደግሞ በመስጊድ ውስጥ ሲሰግድ ግጭቱ በመነሳቱ እዚያው ቆይቶ እያለ አድማ በታኝ ፖሊስ ሲመጣ አባል መሆኑን ሲያሳይ፣ «ውስጥ ለምን ገባህ? ፖሊስ ሆነህ እንዴት እዚህ ልትገባ ቻልክ?» ተብሎ መታሰሩን ገልጿል። «ፖሊስ በመሆኔ ነው የታሰርኩት» የሚለው ኢንስፔክተር መሐመድ፣ አንድ ሰው ወንጀል ከሠራ መጠየቅ እንዳለበት ተናግሮ፣ እሱ የተያዘበት ሁኔታ እንኳን ለእስር ሊያበቃው ቀርቶ ምስክርነት መስጠት የማይችልበት ሁኔታ ላይ እንደነበረ ገልጿል። ምክንያቱ ደግሞ እሱ የነበረው በመስጊድ ውስጥ መሆኑና ብጥብጡ የነበረው ከመስጊድ ውጪ በመሆኑ ነው። ፖሊስ ሆኖ በመስጊድ ውስጥ ወይም አካባቢ መገኘት የማይቻል ከሆነ፣ ይህንን እንደ ትምህርት እንደሚወስደው በመናገር በዋስ ከእስር ተለቆ፣ ወደፊት የሚጠየቅበት ጉዳይ ካለ ሥራውን እየሠራ እንዲጠባበቅ ፍርድ ቤቱን ጠይቋል።

ምክትል ኢንስፔክተር አደምም መስጊድ ውስጥ እንደነበረና የተያዘው ብጥብጡ ካበቃ በኋላ ከቀኑ አሥር ሰዓት ላይ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ገልጾ እሱም፣ «የታሰርኩት ፖሊስ በመሆኔ ነው። ከተያዝኩበት ቦታ እስከ ጣቢያ ድረስ የተወሰድኩት እየተመታሁ ነው። ለ19 ቀናት ታስሬያለሁ። ቤቴ ተፈትሾ ምንም የተገኘ ነገር የለም። ሙስሊም በመሆኔ ብቻ መጠየቅ የለብኝም፤» ካለ በኋላ ዋስትና ሊፈቀድለት እንደሚገባ ፍርድ ቤቱን ጠይቋል።

ቀድሞ ትሠራ የነበረው የፀጥታ (ኢንተለጀንስ) ሥራ እንደነበርና በነበራት ተገቢ ያልሆነ ባህሪ ቢሮ ውስጥ እንድትሠራ መደረጓን በመርማሪ ፖሊሶች ለፍርድ ቤት የተነገረላት ምክትል ሳጅን ሳሊና መሐመድ፣ የተጠረጠረችበትን ድርጊትና ፖሊስ ጊዜ ቀጠሮ እያለ የወሰደውን ረዥም ጊዜ ተቃውማለች። መርማሪ ፖሊስ መረጃ ለመሰብሰብ ከበቂ በላይ ጊዜ መውሰዱንና የፌዴራል ፖሊስ በብጥብጡ ዕለት የቀረፀውን የቪዲዮ ማስረጃ እንዲሰጠው በደብዳቤ ጠይቆ እየተጠባበቀ መሆኑን ለፍርድ ቤት ያስረዳው ተገቢ አለመሆኑን የተቃወመችው ምክትል ሳጅን ሳሊና፣ እሷ የኦዲዮ ቪዥዋል ክፍል ሠራተኛ እንደነበረች በማስረዳት ፖሊስ ለማስረጃ የሚፈልገው ምሥል መኖሩን በደብዳቤ ሲገልጽ በአሥር ደቂቃ ውስጥ ማግኘት እንደሚቻል አስረድታለች። ቤቷን፣ ተንቀሳቃሽ ስልኳንና የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ መርምረውና ፈትሸው ምንም ያገኙባት ነገር እንደሌለ አስረድታ፣ የተሰጠው ቀን ከበቂ በላይ መሆኑን በመጠቆም ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቀድ እንደማይገባ ተቃውማለች።

ፍርድ ቤቱ ለመርማሪ ፖሊስ ተጨማሪ ጊዜ የፈቀደው የተጠርጣሪዎቹን የወንጀል ተሳትፎ በመለየት እንዲያቀርብ፣ በብጥብጡ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ተጎጂዎች ያሉበትን ሁኔታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና ከፖሊስ ሆስፒታል እንዲያቀርብ እንደነበር አስታውሶ መርማሪ ፖሊሶቹ እንዲያስረዱ ጠይቋል። 12 ተጠርጣሪዎች በዕለቱ በሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን፣ ንብረት ማውደማቸውን፣ የደበደቧቸው ፖሊሶችና ሰላማዊ ሰዎች በተለይ በሆስፒታል ኮማ ውስጥ ያሉት መናገር እንደማይችሉ በማስረዳት፣ የተጎዱት ሰዎች ባይድኑ ተጠርጣሪዎቹ ዋስትና በሚከለክለው የሰው መግደል ወንጀል ተጠርጥረው ስለሚከሰሱ ዋስትና እንደሚቃወም አስረድቷል።

የሰማያዊ ፓርቲ አባል የሆነችው ወ/ት ወይንሸት ሞላ፣ ያለምንም ምክንያትና እምነቷ በማይፈቅድላት ቦታ በብጥብጡ ውስጥ መገኘቷንና ብጥብጡን ስታበረታታና የተለያዩ መፈክሮችን የያዙ በራሪ ወረቀቶችን ስትበትን እንደነበር አስረድቷል። የአዲስ ጉዳይ መጽሔት ፎቶ ጋዜጠኛ አዚዛ መሐመድ እምነቷ እስልምና ቢሆንም፣ በሁከቱ ቦታ ተገኝታ ስትመራና ስታግዝ እንደነበር መርማሪ ፖሊስ አስረድቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ስለሆነችውና ስለፎቶ ጋዜጠኛዋ ለፍርድ ቤቱ የሚያስረዳው ሚስጥር እንዳለም መርማሪ ፖሊሱ ገልጿል። ሰነዶችና ምስክሮችን ማሰባሰብ፣ ተጨማሪ ተጠርጣሪዎችን መያዝ፣ ከጥቁር አንበሳና ከፖሊስ ሆስፒታሎች ስለተጎጂዎች መረጃ መቀበል እንደሚቀረው በመግለጽ ተጨማሪ 14 ቀናት የምርመራ ጊዜ እንዲፈቀድለት ለፍርድ ቤቱ አመልክቷል።

ሙስታዝ መንሱር የተባሉ ተጠርጣሪ ደግሞ ያለምንም ምክንያት መታሰራቸውን ገልጸው፣ ከሚመለከታቸው ተቋማት ሰላማዊ ሰው ስለመሆናቸው ማስረጃ እንደተጻፈላቸው፣ ሙስሊሙ ኅብረተሰብን በማስተማር የሚያረጋጉ ከመሆናቸው ውጪ ምንም ያደረጉት ነገር እንደሌለ በማስረዳት፣ «እኔ በዋስ ሳይሆን በነፃ መሰናበት አለብኝ፤» በማለት ፍርድ ቤቱን ጠይቀዋል።

የሰማያዊ ፓርቲ አባሏ ወ/ት ወይንሸትም ለፍርድ ቤቱ ባቀረበችው አቤቱታ፣ መርማሪዎቹ የወሰዱት የምርመራ ጊዜና ምርመራ በቂ መሆኑን አስረድታለች። «የፖለቲካ ፓርቲ አባልና ወደፊትም የሴት መሪ እንደመሆኔ መጠን ሁኔታውን ለመታዘብ በሥፍራው ተገኝቻለሁ። የመንግሥት አካላት ለይተው ስለሚያውቁኝ ነው የተያዝኩት። በራሪ ወረቀት በትናለች መባሉ ፍፁም ሐሰት ነው፤» ስትል አስረድታ፣ በዋስ እንድትለቀቅ ፍርድ ቤቱን ጠይቃለች። የአዲስ ጉዳይ መጽሔት ፎቶ ጋዜጠኛ አዚዛ መሐመድም ለፍርድ ቤቱ እንዳስረዳችው ወደ ሥፍራው የሄደችው ሥራዋን ለመሥራት ነው። የትኛውንም ወገን ደግፋና አቋም ይዛ አለመሄዷን አስረድታለች።

## የአርባ ምንጭ ከተማ የሰማያዊ ፓርቲ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አንዳንድ ወገኖች የአሁኑን እስር ከመጪው ምርጫጋር እያያዙት ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ የሚታየው የኑሮ ውድነትና የፍትህ እጦት በህዝቡ ዘንድ የፈጠረውን ስሜት ተቃዋሚዎች እንዳይጠቀሙበት አስቀድሞ የመከላከል እርምጃ እየተወሰደ ነው ይላሉ። በሌላ ዜና ደግሞ ዋስትና የተፈቀደላቸው ሙስሊም ፖሊሶችና የሰማያዊ ፓርቲ አባሏ ወ/ት ወይንሸት ሞላ እንደገና እንዲታሰሩ ተደርጓል። ሪፖርተር እንደዘገበው በአንዋር መስጊድ ውስጥ በቅርቡ ተፈጥሮ የነበረውን ግጭት አስተባብረዋል ተብለው የታሰሩ ሙስሊም የፖሊስአባላት፣ የታሰሩት የአድማ በታኝ ፖሊስ አባላት መሆናቸውን መታወቂያ በማሳየታቸው ብቻ መሆኑን ለፍርድ ቤት ተናግረዋል።

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጊዜ ቀጠሮ ማስቻያ ችሎት ለአራተኛ ጊዜ በቀረቡበት ወቅት በግጭቱ አለመሳተፋቸውን ተናግረዋል። ኮንስታብል አብዱራህማን ወንድሙን ለመጠየቅ በመሄደበት ጊዜ፣ የፀሎት ሰዓት ስለደረሰበት አንዋር መስጊድ ሰግዶ በመመለስ ላይ እንዳለ መያዙን ገልጿል። ኢንስፔክተር መሐመድ የሱፍ ደግሞ በመስጊድ ውስጥ እየሰገደ በነበረበት ወቅት ግጭቱ በመነሳቱ እዚያው መቆየቱንና መታወቂያውን ለአንድ የፖሊስ አባል ሲያሳይ« ውስጥ ለምንገባህ? ፖሊስ ሆነህ እንዴት እዚህ ልትገባ ቻልክ?» ተብሎ መያዙን ገልጿል።

ኢንስፔክተር ሙሃመድ እሱ በመስጊድ ውስጥ ባለበት ጊዜ ከውጭ ብጥብጥ መነሳቱን ገልጾ፣ እንኳንስ ለክስ ይቅርና ለምስክርነት እንደማይበቃ ገልጿል። “ፖሊስሆኖ በመስጊድ ውስጥ ወይም አካባቢ መገኘት የማይቻል ከሆነ ይህንን እንደትምህርት እንደሚወስደው በመናገር በዋስ ከእስር ተለቆ፣ ወደፊት የሚጠየቅበት ጉዳይ ካለ ሥራውን እየሠራ እንዲጠባበቅ ፍርድ ቤቱን” መጠየቁን ጋዜጣው ዘግቧል። ሌላው እስረኛ ምክትል ኢንስፔክተር አደም መስጊድ ውስጥ እንደነበረና ብጥብጡ ካበቃ በኋላ ከቀኑ አሥር ሰዓት ላይ መያዙን ገልጾ፣ ፖሊስ በመሆኑ ብቻ መያዙን እንዲሁም ከተያዝኩበት ቦታ እስከ ጣቢያ ድረስ እየተደበደበ መወሰዱን” ተናግሯል። ለ19 ቀናት መታሰሩን፣ ቤቱ ሲፈተሽ ምንም ነገር አለመገኘቱን፣ ሙስሊም በመሆኑ ብቻ መጠየቅ እንደሌለበት አስረድቷል።

ከዚህ ቀደም የፀጥታ (ኢንተለጀንስ) ሥራስትስራ እንደነበርና ተገቢ ያልሆነ ባህሪ በማሳየቷ ቢሮ ውስጥ እንድትሠራ መደረጓን በመርማሪፖ ሊሶች ለፍርድ ቤት የተነገረላት ምክትል ሳጅን ሳሊና መሐመድ፣ ፖሊስ ለምርምራ በሚል የሚወስደውን የጊዜ ቀጠሮ ተቃውማለች። እንደ ጋዜጣው ዘገባ ሳጅን ሳሊና “መርማሪ ፖሊስ መረጃ ለመሰብሰብ ከበቂ በላይ ጊዜ መውሰዱንና የፌዴራል ፖሊስ በብጥብጡ ዕለት የቀረፀውን የቪዲዮማስረጃ እንዲሰጠው በደብዳቤ ጠይቆ እየተጠባበቀ መሆኑን ለፍርድ ቤት ያስረዳው ተገቢ አለመሆኑን” ተናግራለች። እሷ የኦዲዮቪዥዋል ክፍል ሠራተኛ እንደነበረች በማስረዳት ፖሊስ ለማስረጃ የሚፈልገው ምሥል መኖሩን በደብዳቤ ሲገልጽ በአሥር ደቂቃ ውስጥ ማግኘት እንደሚቻል አስረድታለች። ቤቷን፣ ተንቀሳቃሽ ስልኳንና የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ መርምረውና ፈትሸው ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የአርባ ምንጭ ከተማ የሰማያዊ ፓርቲ

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

ምንም ያገኙባት ነገር እንደሌለ አስረድታ፣ የተሰጠውቀን ከበቂ በላይ መሆኑን በመጠቆም ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቀድ እንደማይገባ ተቃውማለች።

”ፖሊስ ከፍርድ ቤት ለቀረበለት ጥያቄ፣” ፖሊስ 12 ተጠርጣሪዎች በዕለቱ በሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን፣ ንብረት ማውደማቸውን፣ የደበደቧቸው ፖሊሶችና ሰላማዊ ሰዎች በተለይ በሆስፒታል ኮማ ውስጥ ያሉት መናገር እንደማይችሉ በማስረዳት የተጎዱት ሰዎች ባይድኑ ተጠርጣሪዎቹ ዋስትና በሚከለክለው የሰው መግደል ወንጀል ተጠርጥረው ስለሚከሰሱ ዋስትና እንዳይፈቀድላቸው” ጠይቋል። የሰማያዊ ፓርቲ አባል የሆነችው ወ/ት ወይንሸት ሞላ፣ እምነቷ በማይፈቅድላት ቦታ በብጥብጡ ውስጥ መገኘቷንና ብጥብጡን ስታበረታታና የተለያዩ መፈክሮችን የያዙ በራሪ ወረቀቶችን ስትበትን እንደነበር ፖሊስ ገልጿል። የአዲስ ጉዳይ መጽሔት ፎቶ ጋዜጠኛ አዚዛ መሐመድ እምነቷ እስልምና ቢሆንም፣ በሁከቱ ቦታ ተገኝታ ስትመራና ስታግዝ ነበር ሲል መርማሪ ፖሊስ ለፍርድ ቤቱ ተናግሯል የሰማያዊ ፓርቲ አባሏ ወ/ት ወይንሸት መርማሪዎቹ የወሰዱት የምርመራ ጊዜ በቂ መሆኑን ተናግራለች። ወይንሸት በፖሊስ የቀረበውን ውንጀላ አስተባብላለች። ጋዜጠኛ አዚዛ መሐመድም ወደ ሥፍራው የሄደችው ሥራዋን ለመሥራት ብቻ መሆኑን ተናግራለች። ፍርድ ቤት በመጨረሻም ተጠርጣሪ ሙስታዝ መንሱር፣ የሰማያዊ ፓርቲ አባል ወ/ት ወይንሸት ሞላና የአዲስ ጉዳይ መጽሔት ፎቶጋዜጠኛ አዚዛ መሐመድ እያንዳንዳቸው በአምስት ሺሕ ብር ዋስ እንዲለቀቁ በማዘዝ፣ በሌሎቹተ ጠርጣሪዎች ላይ የስምንት ቀናት ጊዜ በመፍቀድ ለነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል። ሦስቱተ ጠርጣሪዎች በአምስት ሺሕ ብር ዋስ እንዲፈቱ ፍርድ ቤቱ ቢወስንም፣ መርማሪ ፖሊስ በሰዓታት ልዩነት ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝአቅርቦ፣ ‹‹ይፈቱ›› የሚለውን ውሳኔ በማሻር በሦስቱም ተጠርጣሪዎች ላይ ተጨማሪ የሰባት ቀናት የምርመራ ጊዜ ጠይቆ ተፈቅዶለታል።